**ለ2013 በትም/ቤት ክሊኒኮች ለሚከናወነው የፍሉ ክትባት ይመዝገቡ።**

የMontgomery County የጤናና ህዝባዊ አገልግሎት መምርያ በኖቨምበር ወር እድሜአቸው 18 እና ከዚያ በታች ለሆኑ ልጆች በተለያዩ የMCPS ትም/ቤቶች ነፃ በአፍንጫ የሚረጭ የፍሉ ክትባት ህክምና (FluMist) ያካሂዳል።

አርብ ኖቨምበር 1፣ ካውንቲው የፍሉ ህክምናዎች በJohn F. Kennedy፣ Richard Montgomery እና Seneca Valley 2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች ያከናውናል። እለቱ የመምህራን የባለሙያዎች ቀን ስለሆነ በዚያን እለት ትምህርት አይኖርም። ህክምናዎቹ ለማንኛውም በትምህርት እድሜ ውስጥ ለሚገኝ ልጅ ክፍት ይሆናሉ።

ሁሉም የMCPS ኤሌሜንታሪ ትም/ቤቶች ሰኞ ኖቨምበር 11 ወይም ማክሰኞ ኖቨምበር 12፣ ተማሪዎች በቅድሚያ ከተለቀቁ በኋላ፣ የፍሉ ህክምና ያስተናግዳሉ። ተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ ትም/ቤት ወደ መኖርያ ቤት ይላካል።

ሁሉም ህክምና ነፃ ነው፣ ነገር ግን የክትባት አቅርቦት የተወሰነ ስለሆነ ምዝገባ ያስፈልጋል። ለተጨማሪ መረጃ፣ የMontgomery County የጤና እና የህዝባዊ አገልግሎቶች ድር ጣብያ ይጎብኙ።

**ስለ ወጣትና እፅ ውይይት ይቀላቀሉን**

Montgomery County Public Schools (MCPS)፣ ከካውንቲ እና ከበጎ አድራጎት ሽርኮች ጋር በመሆን፣ ስለ ወጣት የእፅ መማገጥና የመከላከል በሚል ሰኞ ኦክቶበር 7 አንድ የማህበረሰብ መድረክ ያስተናግዳል። ክውነቱ፣ ርእሱ "የመናገር ግዜ፡- የአልኮልና የሌላ እፅ መከላከያ መድረክ" ሆኖ፣ የሚከናወነውም በRichard Montgomery High School, 250 Richard Montgomery Dr. in Rockville፡ ከ6:30 p.m. እስከ 9 p.m. ድረስ ነው።

ክውነቱ የሚቀነባበረው በMCPS፣ የMontgomery County ፖሊስ መምርያ፣ የMontgomery County የትብብር ምክር ቤት፣ የMontgomery County የወጣት የእፅ መማገጥ መከላከያ ማህበር፣ እና Brave and Bold Coalition (የጀግናና የደፋር ህብረት) ነው። ክውነቱ የመገልገያ ትርእይት (fair)፣ የተለያዩ አቅርቦቶች፣ እና የጥያቄና የመልስ ግዜ ይኖረዋል።

በወቅቱ ንግግር ያደርጋሉ ተብለው የሚጠበቁት የበላይ ተቆጣጣሪ ጆሹዋ ስታር እና ሌሎች የMCPS ሰራተኛ አባላት፣ እንዲሁም የሚከተሉትን የሚያጠቃልል የእፅ መማገጥና መከላከል መስክ ሊቃውንት፡-

- Dr. James M. Bjork (ዶ/ር ጄምስ ኤም ቢዮርክ)፣ በNational Institute on Drug Abuse (ብሄራዊ የእፅ መማገጥ እንስቲቱት)፣ የፕሮግራም መኮንን
- Dr. Raymond Crowel (ዶ/ር ሬይሞንድ ክሮወል)፣ በMontgomery County የስነምግባር ጤና እና የቀውስ አገልግሎቶች፣ ሀላፊ
- Sergeant Keith Matthis (ሳጂን ኪት ማቲስ፣ ከMontgomery County ፖሊስ መምርያ

ለመከታተል ፍላጎት ያላቸው [በቅድሚያ እንዲመዘገቡ](#) ይጠየቃሉ።

ለተጨማሪ መረጃ፣ 301-279-3100 ይደውሉ።

በConsortia እና በApplication-Only (ለአመልካቾች-ብቻ) ፕሮግራሞች ፍላጎት አለዎትን?

MCPS የተለያዩ ጠንካራ፣ አሳታፊ እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች ያቀርባል። አንዳንድ ፕሮግራሞች ስፖንሰር ለሚያደርጋቸው ትም/ቤት ተማሪዎች ብቻ ክፍት ናቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ በካውንቲው ለሚገኙ ለሁሉም ተማሪዎች ክፍት ናቸው። እነዚህ ፕሮግራሞች የተለያዩ የመግቢያ መስፈርቶችና የማመልከቻ ሂደቶች አሏቸው። ይህ የመቆጣጠርያ ዝርዝር (checklist) ለልጃቸው/ለልጆቻቸው *Choice (ምርጫ)* ሂደት እና አመልካች-ብቻ ፕሮግራሞች ፍላጎት ላላቸው ወላጆች የተወሰኑ ጠቃሚ መረጃዎች ይሰጣል።

- ✓ ስለ Choice ሂደትና አመልካቾች-ብቻ ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃ የሚከተሉትን ድር ጣቢያዎች ጎብኙ፡-

  [North East Consortium (የኖርዝ ኢስት ህብረት)](#)

  [Down County Consortium (የዳውን ካውንቲ ህብረት)](#)

  [Middle School Magnet Consortium (ሚድል ስኩል ማግኔት ህብረት)](#)

  [አመልካቾች-ብቻ ፕሮግራሞች](#)

- ✓ በኦክቶበር ወር ውስጥ ክፍት የሆኑ ክፍት ስብሰባዎች/በአላት ስለ *Choice* ፕሮግራሞች ለመማር በኖርዝኢስት ህብረት (NEC) እና የዳውንካውንቲ ህብረት (DCC) 2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች ወይም በሚድልስኩል ማግኔት ህብረት የመካከለኛ ደረጃ ትም/ቤት ይከታተሉ/ይሳተፉ። በተጨማሪም አመልካቾች-ብቻ ፕሮግራሞች ይበልጥ ለመማር በከፍተኛ ተስጥኦ ላላቸው ማእከሎች በተለያዩ የኤሌሜንታሪ ትም/ቤቶች እና በRoberto Clemente (ሮቤርቶ ክሌሜንቴ)፣ Eastern (ኢስተርን)፣ እና Takoma Park (ታኮማ ፓርክ) የመካከለኛ ደረጃ ትም/ቤቶች የመረጃ ስብሰባዎች ማዳመጥ ይችላሉ።
  [ቀኖችንና ቦታዎችን ይያዙ](#)

- ✓ የልጅዎን ፍላጎት እጅጉን የሚስማማ ፕሮግራም ላይ ከወሰኑ በኋላ፣ ማመልከቻውን ከ**አርብ ኖቬምበር 8** የግዜ ገደብ በፊት ያስገቡ። የህብረት ትም/ቤቶች (Consortia) ወላጆች የ*Choice* ቅፆች በፖስታ ኦክቶበር አጋማሽ ላይ ያገኛሉ።

- ✓ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች? የ[Special Programs (ልዩ ፕሮግራሞች) ድር ጣብያ](#) ይጎብኙ ወይም 301-592-2040 ይደውሉ።

**ኤዲሰን 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት የማህበረሰብ ትርእይት በአል ያዘጋጃል**

**የቶማስ ኤዲሰን** 2ኛ **ደረጃ የቴክኖሎጂ ትም/ቤት ሁለተኛውን አመታዊ የማህበረሰብ ትርእይት በአል ቅዳሜ ኦክቶበር** 26 ከ9:30 a.m. እስከ 1:30 p.m. **ያከብራል። በክውነቱ የግጥሚያዎች በአል** (carnival games)፣ **አንድ** moon bounce (**የልጆች ዝላይ ድንኳን**)፣ **የፅጥታ ጨረታ እና የመማርያ ክፍል ትርእይቶች ይኖራሉ። አንድ** DJ (**ዲጄይ ሙዚቀኛ**) **እና የምግብ ሽያጭ ይኖራሉ። በአሉ ለሁሉም** የMCPS **ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ክፍት ነው።**

**የበአሉ ገቢዎች በማህበረሰቡ ለ**Career and Technology Education (**ስራና ቴክኖሎጂ ትምህርት**) **ይውላሉ።**

**ኤዲሰን የሚገኘው በ**12501 Dalewood Dr. **በ**Silver Spring **ነው። ለተጨማሪ መረጃ** 301-929-2175 **ይደውሉ።**

**የተማሪ አመራርና የአገልግሎት እድሎች ይገኛሉ**

**ለ**State Student Member on the Board of Education (**በትምህርት ቦርድ የስቴት ተማሪ አባል**)(SMOB) **ቦታ እና በ**Montgomery County Board of Elections Future Vote Initiative (**የወደፊት ምርጫዎች ድምፅ ተነሳሽነት ቦርድ**) **ማመልከቻዎች በመግባት ላይ ናቸው።**

*የስቴት SMOB*

**ለትምህርት ቦርድ የስቴት ተማሪ አባል** (SMOB) **ለ**2014-2015 **የትምህርት አመት መወዳደር የሚፈልጉ የአስረኛና የ**11**ኛ ክፍል ተማሪዎች ከትም/ቤታቸው ርእሰመምህር ጋር እንዲነጋገሩ ይደፋፈራሉ። እያንዳንዱ የ**MCPS 2**ኛ ደረጃ ትም/ቤት አንድ ተማሪ ከየትምቤታቸው ለተመራጭነት ማቅረብ ይችላሉ። ማመልከቻውን ከ**[www.mdstudentcouncils.com](www.mdstudentcouncils.com) **ማግኘት ይቻላል። በማመልከቻው ጥቅል የተዘረዘሩትን የሚከተሉትን የግዜ ገደቦች ተማሪዎች በጥንቃቄ መመልከት አለባቸው።**

**ኦክቶበር** 25 2013:- **የትም/ቤት የተመራጭ ማቅረብያ ቅፅ ገቢ የሚሆንበት**
**ኖቨምበር** 25 2013:- **የተማሪ ማመልከቻ ተሟልቶ በፖስታ የሚላክበት**
**ጅናሪ** 4 2014:- **በ**Maryland State **የትምህርት መምርያ ተወዳዳሪው/ዋ ቃለ መጠይቅ የሚደረግበት ቀን**
**ፌብሩዋሪ** 8 2014:- **የመጨረሻዎቹ አምስት ተመራጮች ለ**Maryland Association of Student Councils Legislative Session (location TBD) (**የተማሪዎች ምክር ቤቶች ማህበር ህጋዊ ስብሰባ ራሳቸውን ያቀርባሉ።**
**ለተጨማሪ መረጃ** Karen Crawford (**ካረን ክራውፎርድ**)**ን ያግኙ።**

***የምርጫ ቀን ቡድን አባል ሁኑ***

የMontgomery County Board of Elections Future Vote Initiative (**የምርጫ ቦርድ የወደፊት ድምፅ ተነሳሽነት**) **የ**2**ኛ ደረጃ ትም/ቤት የ**11**ኛና የ**12**ኛ ክፍል ተማሪዎች በሚመጣው የ**2014 **የስቴት አስተዳዳሪ ምርጫ ዳኞች እንዲሆኑ ይፈልጋል። ዳኛ ሆነው የሚያገለግሉ ተማሪዎች** $180 **ያገኛሉ። የማመልከቻ ገደብ አርብ ኖቨምበር** 1 **ነው። ለተጨማሪ መረጃና ለማመልከቻ፣ ለ**email Dr. Gilberto Zelaya (**ዶ/ር ጊልበርቶ ዘለያ**) **ኢሜይል ያድርጉ።**

Junior Achievement Essay (ጁንየር የግኝት ድርሰት) ውድድር ለ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ተከፍቷል

የ2013 ጁንየር የግኝት ድርሰት ውድድር ከ9-12 ክፍሎች ለሚገኙም ተማሪዎች አሁን ክፍት ነው። ተማሪዎች "የትኛው ነው በሚመጣው 10 አመት ህይወትን በዩናይትድ ስቴትስ የሚያሻሽል፣ የንግድ ስራ ፈጣሪ ወይስ ማህበራዊ ስራ ፈጣሪ?" በሚል አርእስት 1,000-1,500 ቃላት ያለው መጣጥፍ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ለምን? ከሜሪላንድ 3 አሸናፊዎች ተመርጠው የ$10,000 ስኮላርሺፕ ይቀበላሉ ከሜሪላንድ፣ ቨርጂንያ ወይም ዲሲ ታላቅ ሽልማት አሸናፊ የ$20,000 ስኮላርሺፕ ይቀበላል። ተማሪዎች በwww.myja.org/students/essay መስመር ላይ ማመልከት ይችላሉ። ሁሉም መጣጥፎች በሮብ ኖቨምበር 6 ገቢ መሆን አለባቸው።

ለተጨማሪ መረጃJunior Achievement ድር ጣብያ ይጎብኙ።

የኮሌጅ የበአል ወራት ተገባዷል

ለወላጆችና ለተማሪዎች ኦክቶበርና ኖቨምበር የኮሌጅ በአላትና ስለ ከፍትኛ ትምህርት መማርያ እድሎችን በሚመለከት በርካታ እድሎችን ይሰጣሉ። የቅርብ ግዜ ዋና ዋና በአላት በጥቂቱ እነዚህ ናቸው፡-

**የ2013 College Scholarship Conference (የኮሌጅ ስኮላርሺፕ ስብሰባ):- ቅዳሜ ኦክቶበር 26**

Montgomery ኮሌጅ አመታዊውን የኮሌጅ ስኮላርሺፕ ስብሰባ ቅዳሜ ኦክቶበር 26 ከ9 a.m. እስከ 2 p.m. ያካሂዳል። ስብሰባው ስለ ስኮላርሺፖች፣ ፋይናንሳዊ እርዳታ እና የመግቢያ ሂደት መረጃዎች ያቀርባል። ክውነቱ በMCPS እና ሼዲ ግሩቭ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖንሰር የሚደረግ ነው። ለተጨማሪ መረጃና ለመመዝገብ www.montgomerycollege.edu/scholarshipconference ይጎብኙ።

**Greater Washington D.C. National College Fair (ታላቁ የዋሺንግቶን ዲሲ ብሔራዊ ኮሌጅ በአል):- ሮብ ኖቨምበር 6፣** በዋሺንግቶን Washington Convention Center ከ9 a.m. – እኩል ቀን እና 6 – 8 p.m. ተጨማሪ መረጃ በNational Association for College Admission Counseling (የኮሌጅ መግቢያ ብሄራዊ ማህበር) ድር ጣብያ ይገኛል።

**Hispanic College Fair(ሂስፓኒክ ኮሌጅ በአል):- ሮብ ኖቨምበር 13፣** በActivity Center at Bohrer Park, 506 S. Frederick Avenue in Gaithersburg። ስለ ፈቃድ ወረቀትና የመጓጓዣ መረጃ ከትም/ቤታችሁ ኮሌጅና ስራ ማእከል ጋር ተገናኙ። ለወላጆች ማክሰኞ ኖቨምበር 12 ከ7 p.m. – 8:30 p.m Gaithersburg High School, 101 Education Boulevard in Gaithersburg ልዩ የመረጃ ፕሮግራም ተይዟል። ለተጨማሪ መረጃ፣ Patty Maloney በ301-353-8029 ይገናኙ ወይም National Hispanic College Fair ድር ጣብያ ይጎብኙ።